የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ........ 1

የኤጀንሲው ራዕይ........ 2

የኤጀንሲው ተልዕኮ........ 2

የኤጀንሲው አላማ........ 2

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር........ 2

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር........ 4

የሰው ኃይል........ 4

የፋይናንስ ምንጭ........ 5

የኦዲቱ አላማ........ 5

የኦዲቱ ጭብጦች........ 5

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች........ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ........ 6

የአሰራር ፍሰት መግለጫ........ 7

ክፍል ሁለት.

ግኝቶች........ 8

በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ

አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ.

በኤጀንሲው ስለመኖሩና አሰላሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ስለመሆኑ፤........ 8

ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የገቡትን ውል ተፈጻሚ

ባያደርጉ ጉዳያቸውን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል........ 9

የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ መጠቀሱን በተመለከተ፤........ 9

በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግን

ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት ለመሰብሰብ

የሚያስችል በኤጀንሲው የተዘረጋ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት

መኖሩን በተመለከተ፤........ 9

ባለሀብቶች በጨረታ የሚሸጡ የልማት ድርጅቶችን

ተጫርተው ለመግዛት ከጨረታ ሰነዱጋር የሚያቀርቧቸው

ቢዝነስ ፕላኖች የሚገቡትን ግዴታ ለመፈጸም የሚያስችላቸው

ስለመሆኑ በኤጀንሲው የሚደረግ ግምገማ ስለመኖሩ፤........ **Error! Bookmark not defined.**

የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በኤጀንሲው

ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ

መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በተመለከተ፤........ 12

በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች

የተጠናቀረ ዝርዝር መረጃ በኤጀንሲው ስለመኖሩ፤........ 14

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ኃሳቦች 15

ክፍል አራት

የማሻሻያ ኃሳቦች........ 17

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

አባሪ 2

እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም.ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ሂሳብ ያለባቸው የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር መግለጫ

መግቢያ

1. መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ሚናና ተሳትፎ ባገናዘበ መልኩ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን እንዲሁም የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ስር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት በማስፈለጉ እነዚህን አላማዎች ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን በማዋሃድ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 412/1996 ተቋቋመ።

2. የፕራይቬታይዜሽን ሥርዓቱን ለማጠናከርና አፈጻጸሙን ለማፋጠን በመንግስት እጅ የሚገኙ የልማት ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሽያጭም ሆነ በሌሎች የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች ወደ ግል ባለሃብቶች ለማዛወር ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በዚህም እንቅስቃሴ ከ1987-1997 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስር ዓመታት 213 ድርጅቶችንና ቅርንጫፎችን ወደ ግል በማዛወር ብር 3.13 ቢሊዮን ገቢ የተገኘ ሲሆን ፣ ከ1998-2003 ዓ.ም ባሉት ስድስት ዓመታት ደግሞ 97 ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በብር 5.6 ቢሊዮን ወደ ግል ተዛውረዋል። በድምሩ ባለፉት አስራ ስድስት ዓመታት 310 የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በጨረታ ሽያጭና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ግል ተዛውረው ብር 8.7 ቢሊዮን ገቢ ተገኝቷል።

3. ኤጀንሲው በከለሰው የአምስት ዓመት (2003-2007 ዓ.ም) ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት፣ በ2003 ዓ.ም 24 ፣ በ2004 ዓ.ም 9 ፣ በ2005 ዓ.ም 15 በ2006 ዓ.ም 1 እንዲሁም በ2007 ዓ.ም 1 በድምሩ 50 የልማት ድርጅቶችንና ቅርንጫፎችን በቀጥታ ሽያጭ ወደ ግል የማዛወር ግብ ይዟል።

4. ስለሆነም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭና ሌሎች የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች የሚገኘው ገቢ ከፍተኛ በመሆኑ ገቢው በትክክል መሰብሰቡን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ይህ የክዋኔ ኦዲት እንዲከናወን ተደርጓል።

የኤጀንሲው ራዕይ

5. ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች እየተፈጠሩ ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ አሰራር ወደ ግል ተዛውረው ማየት፣

የኤጀንሲው ተልዕኮ

6. የልማት ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን ውጤት እያስገኙ ወደ ግል ይዞታ እንዲተላለፉ ማድረግ፣

የኤጀንሲው አላማ

7. ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-
   - የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ መሰረት የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም ማድረግ፣
   - የመንግስት የልማት ድርጅቶች አቅማቸውን በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ በማስቻልና የተሻሻሉ የማኔጅመንት ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና የላቀ ውጤት እንዲያመጡ ማገዝ፣
   - በተለያዩ ምክንያቶች የግል ባለሃብቶች ሊሳተፉባቸው ባልቻሉ ለኢኮኖሚው አጠቃላይ ልማት ማነቀ ሊሆኑ በሚችሉ ዘርፎች አዳዲስ የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
   - የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አመራር መቆጣጠር እና
   - በመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማኅበራት የመንግስትን የባለቤትነት መብት ማስከበር፡፡

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

8. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 412/1996 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   - የፕራይቬታይዜሽንን ፕሮግራም ማስፈጸም፣
   - ወደ ግል የሚዛወሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችንና የአክስዮን ይዞታዎችን ዝርዝር ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ማስወሰን፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ እንዲከናወኑ ማድረግ፣
- በፕራይቬታይዜሽን የሚሳተፉ ባለሃብቶች የሚወዳደሩባቸውን መመዘኛዎች መወሰን ፣ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ተሳትፎም ሊበረታታ የሚችልበትን መንገድ መቀየስ፣
- ፕራይቬታይዜሽኑን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣
- የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙና አፈጻጸሙ በህዝብ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትል በማድረግ በፕራይቬታይዜሽኑ የተሳተፉ ባለሃብቶች የገቧቸውን ግዴታዎች ማክበራቸውን ማረጋገጥ ፣ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት መገምገም፣
- ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ሃሳቦች ገምግሞ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቅርቦ ማጸደቅ ፣ ተግባራዊነታቸውንም መከታተል፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚረዱ ጥናቶችን በማካሄድ አጠቃላይ መመሪያዎችን መስጠት፣
- ለመንግሥት የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን መመደብ ፣ ማንሳት ፣ አበላቸውን መወሰን፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የውጭ ኦዲተሮች ምደባ ማጽደቅ፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ ግቦችና የኢንቨስትመንት እቅዶችን ማጽደቅ፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም መከታተልና መገምገም፣
- በውጭ ኦዲተሮች የተመረመሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ ሪፖርት ማጽደቅ፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ማዋሀድ ወይም መከፋፈል ሲያስፈልግ ተገቢውን ጥናት አካሂዶ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣

- ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድና የማኔጅመንት አባላት ተፈጻሚ የሚሆን በውጤት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፣ በሥራ ላይ እንዲውልም ማድረግ፣
- በአክስዮን ማህበራት የባለአክሲዮኖች ጉባኤ መንግሥትን መወከል ፣ በመንግሥት በኩል የሚቀርቡ የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ አባላትን መሰየም፣
- በሕግ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኞችንና የማኔጅመንት አባላትን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለሚቆዩበት ሁኔታ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት እና
- የንብረት ባለቤት መሆን ፣ ውል መዋዋል ፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ ናቸው።

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር

9. የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፕራይቬታይዜሽን ቦርድ የሚተዳደር ሆኖ ፣ ተጠሪነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው። ኤጀንሲው አንድ ዋና ዳይሬክተር ያለው ሲሆን ፣ ዋናው ዳይሬክተር በስሩ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለትም የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም ሰባት ዳይሬክቶሬቶች ማለትም የዕቅድና የመረጃ ሥራ አመራር ፣ የአሠራር ማሻሻያና የሰው ሃብት ፣ የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ፣ የህግ ፣ የኦዲት ፣ የፋይናንስና አቅርቦት እና የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ። በኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥር የኮርፖሬት አመራር እና የኮርፖሬት አቅም ግንባታና ድጋፍ ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም የፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስር የፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ እና የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ።

<u>የሰው ኃይል</u>

10. በአጠቃላይ ለኤጀንሲው ሚያዚያ 25 2004 ዓ.ም በተፈቀደው የስራ መደብ መሰረት 323 ቋሚ ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን ፣ 204 ቋሚ 2 ኮንትራት በድምሩ 206 ሠራተኞችና 117 ክፍት የስራ መደብ ያለው መሆኑ ታውቋል።

የፋይናንስ ምንጭ

11. የኤጀንሲው የገቢ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት ብቻ ሲሆን ፣ የገቢና የወጪ መግለጫው በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ገቢና ወጪ	2003 ዓ.ም.	2004ዓ.ም.	2005ዓ.ም.
1.	መደበኛ በጀት	8,925,689.85	15,202,804.15	18,476,460.51
2.	መደበኛ ወጪ	8,463,782.10	11,770,526.93	15,804,092.13
3.	ስራ ላይ የዋለው በመቶኛ	94.82	77.4	85.5

የኦዲቱ አላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ አሰባሰብ ወቅቱን ጠብቆ በትክክል የተሰበሰበ መሆኑን ፣ በአሰባሰቡ ሂደት ላይ የተዘጋጁ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ፣ የተዘረጋው የክትትልና የድጋፍ ሥርዓትም ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሣብ አቅርቦ ኤጀንሲው የተሻለ አሰራር እንዲኖረው በማገዝ ተጠያቂነትን ማስፈንና የመሥሪያ ቤታችንን የክዋኔ ኦዲት አላማ ማሳካት ነው፡፡

የኦዲቱ ጭብጦች

13. "በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ" ላይ ሊከናወን ለታቀደው የክዋኔ ኦዲት ሁለት የኦዲት ጭብጦችና ሁለት ንዑስ የኦዲት ጭብጦች ተለይተዋል እነርሱም:-
    1. በኤጀንሲው በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ

ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

1.1. ኤጀንሲው የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ አዋጅና ደንቡን መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣቱንና በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እንዲሁም በኤጀንሲውና በባለሀብቱ መካከል ግንኙነት የሚፈጥሩ ሰነዶች ትክክለኛና ወቅታዊ መሆናቸውን መገምገም፡፡

1.2. ኤጀንሲው በሽያጭ ወደ ግል የተላለፉ የልማት ድርጅቶች ሂሳብን ባለሀብቶቹ በገቡት የሽያጭ ውል መሰረት ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል ፣ ለመቆጣጠርና ያለባቸውን ቀሪ ክፍያ አጠቃለው ማስገባታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

2. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ ከገዙ ባለ ሃብቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥና መደበኛ የመወያያ መድረክ እንዲኖር የዘረጋውን የአሰራር ስርዓትና ተግባራዊነቱን መገምገም፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

14. ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት የኦዲት ጭብጦችና ሁለት ንዑስ የኦዲት ጭብጦች ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል ሃያ አምስት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ አንድ ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ በክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በዋነኛነት በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ከ2003-2005 በጀት ዓመት በተሰሩ ሥራዎች ላይ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣ ከተጠቀሱት በጀት ዓመታት በፊትም በኦዲት አካባቢው ዙሪያ በኤጀንሲው የተከናወኑትን ስራዎች በማካተት ነው፡፡

16. የኦዲት ሥራውም ያተኮረው "በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ" ላይ ሆኖ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብና በአማራ ክልል ባሉ ከተሞች የሚገኙ በተራዘመ ክፍያ በጨረታ የተሸጡ አስራስምንት የልማት ድርጅቶችን በናሙና በመምረጥ የድርጅቶቹን ፋይልና በኤጀንሲው የሚገኙ ከኦዲት ስራው ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስና ድርጅቶቹን በተራዘመ ክፍያ ለገዙ ባለሀብቶች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃዎችን በመሰብሰብ ነው፡፡

የአሰራር ፍሰት መግለጫ

17. **የፕራይቬታይዜሽን ንዑስ የሥራ ሂደት ዳይሬክቶሬት**

- የፕራይቬታይዜሽን ማስፈፀሚያ ዕቅድና መርሀ ግብር ያዘጋጃል ፣ ይፈጽማል፣
- ወደ ግል የሚተላለፉ ድርጅቶችን በሚዲያ ያስተዋውቃል፣
- የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማስተላለፍ የዋጋ ትመና ያዘጋጃል፣
- ድርጅቶቹን ለጨረታ ያቀርባል/ጨረታውን ይገመግማል ፣ ውጤቱን ያስፀድቃል፣
- ለድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ፓርትነር ያፈላልጋል ፣ ያስገባል፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በቀጥታ ሽያጭ ወይም በፓርትነርሽፕ ወደ ግል ያስተላልፋል፣
- ወደ ግል የተላለፉ ድርጅቶችን ርክክብ ያስፈጽማል፣
- ወደ ግል የተላለፉ ድርጅቶችን የቢዝነስ ፕላንና እና የውል አፈፃፀም ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
- ወደ ግል በተላለፉ ድርጅቶች በ20/45 ዘላቂ ጡረታ የሚወጡ ሠራተኞችን ጉዳይ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ከገዙ ወይንም ከተከራዩ ባለሀብቶች የሚፈለጉ ተሰብሳቢ ክፍያን ያስፈጽማል፣
- የፋይዳ ጥናት በማካሄድ ፕራይቬታይዜሽን ያመጣውን ለውጥ ይገመግማል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

<u>በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ በኤጀንሲው ስለመኖሩና አሰላሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ስለመሆኑ፤</u>

18. በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ የጸደቀ የአሰራር መመሪያ ሊኖር ፣ ሂሳብ አሰላሉ መመሪያውን የተከተለና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

19. ይሁንና በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ ኤጀንሲው ለሂሳብ አሰላል የሚጠቀመው የሽያጭ ውልና በተለያየ ጊዜ የጸደቀ የአሰራር መመሪያ ቢኖረውም አንድ ወጥ የሆነና ተቀናብሮ የጸደቀ አለመሆኑ እንዲሁም አሰላሉን የሚያግዝ ዘመናዊ ሶፍትዌር አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

20. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በሰጡት መልስ ፣ የሽያጭ ውል ስምምነቱና በተለያየ ጊዜ የወጣው የአሰራር መመሪያ ስሌቱን ለማከናወን በቂ መረጃ እንደሚሰጥ ነገር ግን ተበታትነው የሚገኙ የአሰራር መመሪያዎች ተሰባስበው አንድ ወጥ መመሪያ ማዘጋጀት እንደሚገባቸው እንዲሁም ስሌቱ በዘመናዊ ሶፍት ዌር መታገዝ እንዳለበት የሚያምኑበት መሆኑንና በ2006 በጀት ዓመት በጀት ተይዞለት ጉዳዩ በሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

21. ስለሆነም የሂሳብ አሰላሉን በተመለከተ የተዘጋጁትን መመሪያዎች አንድ ወጥ አድርጎ ማዘጋጀትና ስራውን በሶፍትዌር ለማገዝ ያለውን ጅምር ስራ አፈጻጸሙን ማፋጠን ከኤጀንሲው ይጠበቃል፡፡

<u>ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የገቡትን ውል ተፈጻሚ ባያደርጉ ጉዳያቸውን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ መጠቀሱን በተመለከተ፤</u>

22. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ለሚሸጣቸው ድርጅቶች የሚያዘጋጀው ውል አስፈላጊ የውል ግዴታዎችን መያዝና በውሉ መሰረት ባይፈጸም ጉዳዩን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ሁሉም የልማት ድርጅቶች ፣ የሚፈለግባቸውን አመታዊ ክፍያ በገቡት ውል መሰረት ባይፈጽሙ ጉዳያቸው ወደ ህግ የሚሄድበት የጊዜ ገደብ በውሉ ውስጥ አልተካተተም፡፡

24. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊ በሰጡት መልስ ፣ የጊዜ ገደቡ በውሉ ያልተቀመጠ ቢሆንም የረጅም ጊዜ ክፍያ በወቅቱ ባለመከፈሉ የሚያስከትለው ከፍተኛ ቅጣት በውሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ገዢን ጠርቶ በማወያየት ባጋጠሙ ችግሮች ላይ የመፍትሔ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ክፍያው እንዲሰበሰብ ጥረት እንደሚደረግና ተፈጻሚ ባይሆን ጉዳዩ ወደ ህግ እንደሚመራ ፣ በድህረ-ፕራይቬታይዜሽን የአሰራር ማኑዋል ክፍያው በወቅቱ ሳይከፈል ሲቀር ፣ ሂደቶችን አልፎ ከ75ኛው ቀን በፊት ወደ ህግ እንዲመራ እንደ አሰራር እንደተቀመጠ እና በኦዲቱ አስተያየት መሰረት የውሉ አካል ከማድረግ ይልቅ መመሪያ ማዘጋጀት ለአሰራር እንደሚያመች ገልጸዋል፡፡

25. በመሆኑም ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ የገዙ ሁሉም ባለሀብቶች ክፍያቸውን በወቅቱ ባይፈጽሙ ወጥ በሆነ አሰራር እንዲጠየቁ ለማድረግ ኤጀንሲው የጊዜ ገደቡን በተመለከተ መመሪያ አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን ቢከታተል የተሻለ አሰራር ይፈጥራል፡፡

<u>በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግን ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል በኤጀንሲው የተዘረጋ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤</u>

26. በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት እንዲከፍሉ ኤጀንሲው በቂ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግና በወቅቱ መክፈል

ላልቻሉትም መክፈል ያልቻሉበትን ምክንያት አጥንቶ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

27. በተራዘመ ክፍያ የልማት ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የሚፈለግባቸውን ቀሪ ሂሳብ በወቅቱ እንዲከፍሉ ኤጀንሲው የሚያደርገው ክትትል ስለመኖሩ በኦዲቱ ሲጣራ ፣ አመታዊ የክፍያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት እንዲፈጽሙ ለማስታወስ በደብዳቤ ፣ ቦታው ድረስ ሄዶ በመጎብኘትና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ከሠነዶችና ለባለሀብቶች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

28. በተጨማሪም ቀሪ እዳን ከመክፈል አንጻር በታዩ ችግሮች ዙሪያ ለባለሀብቶች መጠይቅ በመበተን ኤጀንሲው ጥናት ማድረጉን ህዳር 2005 ዓ.ም ከቀረበ ሪፖርት መረጃ ተገኝቷል፡፡

- ይህም ሆኖ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽመው ውል ከገቡ በኋላ ቀሪ ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት ያላጠናቀቁ ድርጅቶች ስለመኖራቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም. ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ከሃያ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ እና ከሁለት እስከ አምስት አመት የዘገየ ሂሳብ ብር 362,394,242.11 (ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) እና ፓውንድ 300,318.06 (ሶስት መቶ ሺህ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ከዜሮ ስድስት ፓውንድ) በፋይናንስ ሌጀር ተመዝግበው ከሚገኙ ባለሀብቶች የሚፈለግ ነገር ግን በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ መረጃው በአባሪ ሁለት ተያይዟል፡፡

29. በመሆኑም በናሙና ከተመረጡት አስራ ስምንት ድርጅቶች ውስጥ በንጽጽር ከፍተኛ እዳ የተመዘገበባቸውን ስድስት ድርጅቶች በመለየት የግል ማህደሮቻቸውን በመከለስና ለባለሀብቶቹ ቃለመጠይቅ በማቅረብ እዳቸውን በወቅቱ ያልከፈሉበትን ምክንያትን ለማጣራት እንደተቻለው፣

- የቦሌ ቡልቡላ ጠጠር ማምረቻ ድርጅት ባለሀብቱ አክስዮን ማህበሩን ሲገዛ ፣ በአክስዮን ማህበሩ ስም የተመዘገቡ የመሬት ይዞታዎችን የመጠቀም መብት ለገዢው

የተላለፈለት ቢሆንም ፣ ለጠጠር ማምረቻ እንዲሆን የተረከበው ቦታ ለኮንዶሚኒየም ግንባታ በመዋሉ በዚሁ ጉዳይ ክርክር ላይ መሆኑን፣

- አዲስ አበባ ራስ ሆቴል ፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከቀረቡት የንብረት ዝርዝሮች ውስጥ በንብረት ርክክብ ወቅት በብልጫ ለተገኘ የርክክብ ልዩነት ክፍያ ብር 7,745,069.00 ባለሀብቱ እንዲከፍል ኤጀንሲው ጥያቄ ቢያቀርብም ብር 4,959,895.00 ባለሀብቱ ሆቴሉን ከመረከቡ በፊት ለተወሰኑ የመኝታ ክፍሎች እድሳት የወጣ በመሆኑና ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት ክፍሎቹ የታደሱ መሆናቸውን አይቶ በመሆኑ የእድሳት ወጪው ሂሳብ እንደማይመለከተው ጥያቄ ያቀረበ መሆኑ፣
- ኢትዮጵያ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ ፣ ለምርት የሚሆኑ በርካታ ግብዓቶችን ከገዛ በኋላ ለማምረት የመብረትኃ ይል አቅርቦት እጥረት ያጋጠመው መሆኑ፣
- ኮኮብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት በጨረታ ሰነዱ ላይ በዝርዝር የተቀመጡና የንብረት ርክክብ ቆጠራ ሲደረግ ያልተገኙ ንብረቶች በመኖራቸው ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት ይኖረኛል ብሎ የገመተውና የተረከበው ንብረት ባለመጣጣሙ ልዩነቱ ከእዳዬ ላይ ይቀነስልኝ በሚል ለኤጀንሲው የሚያቀርባቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ምላሽ ያላገኘ ስለመሆኑ ከማህደሩ በተገኘ መረጃ የታየ መሆኑ እንዲሁም፣
- የኮኮብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካን ፣ የሀዋሳ ዱቄት አክስዮን ማህበርን እና የታቦር ሴራሚክ አክስዮን ማህበርን የገዙት አንድ ባለሀብት ናቸው፡፡ ባለሀብቱ ድርጅቶቹን ሲጫረቱ ባቀረቡት ቢዝነስ ፕላን መሰረት ሰላሳ በመቶ የራሳቸውንና ሰባ በመቶ ከባንክ ለስራ ማስኬጃ በሚያገኙት ብድር ሰርተው ሂሳቡን ሊከፍሉ ታሳቢ በማድረግ ሲሆን ፣ ነገር ግን ውሉ ባለሀብቱ የመጨረሻውን ሂሳብ ከፍለው ሳይጨርሱ በድርጅቶቹ ላይ የባለቤትነት መብት እንደማይኖራቸው ስለሚጠቅስ ፣ ባለሀብቱ ለስራ ማስኬጃ ብድሩን ከባንክ ባለማግኘታቸው ክፍያውን በወቅቱ መክፈል ያልቻሉ መሆኑ፣

  ለክፍያው መዘግየት በምክንያትነት የቀረቡ ናቸው፡፡

30. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በሰጡት መልስ ከድርጅቶቹ የሚፈለገው ቀሪ እዳ እንዳለ የሚታወቅ መሆኑንና ገንዘቡን ለማሰባሰብ በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥረት ተደርጎ ከአቅም በላይ የሆኑትን በህግ ክትትል እየተደረገ የሚገኝና በዚሁ መሰረት

ከተጠቀሱት 30 ድርጅቶች ውስጥ 7ቱ በፍርድ ቤት በክስ ላይ የሚገኙና ወደአፈጻጸም የተሸጋገሩ 23ቱ ደግሞ የክስ ሂደታቸው ተጀምሮ በህግ የተያዘ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

31. ሆኖም ከባለሀብቶቹ የሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ ከፍተኛ በመሆኑ ኤጀንሲው አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ቀሪ እዳው በአስቸኳይ እንዲሰበሰብ ማድረግ አለበት፡፡

የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በተመለከተ፤

37. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በሚያቀርባቸው የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎችን ትክክለኛነት ሰነዱ ለባለሀብቱ ከመቅረቡ በፊት ማረጋገጥ አለበት፡፡

38. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት አስራ ስምንት ድርጅቶች መካከል የንብረት ርክክብ በሚደረግበት ወቅት የንብረት ቆጠራው በጨረታ ሰነዱ ላይ ከቀረበው የንብረት ዝርዝር ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጉድለት የታየባቸው ሁለት ድርጅቶች ሲሆኑ ፣ እነርሱም

- የኮኮብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ በቁጥር 464 የቢሮ መገልገያ እቃዎች ፣ 5 ማሽነሪዎች ፣ 487 ቱልሶች እንዲሁም 7 ተሽከርካሪዎች በርክክብ ወቅት በተደረገው ቆጠራ ያልተገኙ መሆናቸው፤
- የአዲስ አበባ ራስ ሆቴል በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ በቁጥር አንድ ሚትስቡሽ መኪና(3 ሰው ወይም 12 ኩንታል የመጫን አቅም ያለው) ፣ 1 ቱልስ ፣ 159 የቢሮ እቃዎችና የመገልገያ መሳሪያዎች ፣ 12 የወዳደቁ ንብረቶች ፣ ሁለት ማሽነሪዎች በርክክብ ወቅት በተደረገው ቆጠራ ያልተገኙ መሆናቸው ፤ በኤጀንሲው ከሚገኝ የድርጅቶቹ ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

39. በተጨማሪም ለተገኘው የንብረት ርክክብ ጉድለት ባለሀብቶቹ በጨረታ ሰነድ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተው በብልጫ የተገኙትን ንብረቶች ልዩነቱን እንዲከፍሉ ከተጠየቁት ሂሳብና ከቀሪ ክፍያቸው ላይ ማካካሻ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም ፣ በጉድለት ለተገኙ ንብረቶች ተመላሽ እንዲሆን ወይም ማስተካከያ እንዲሰራ በውል ስምምነቱ ስላልተካተተ ማስተካከያውን ለመስራት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩ ተገልጾ የተጻፈ መረጃ ተገኝቷል፡፡

40. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊ በሰጡት መልስ ፣ የልማት ድርጅቶች ወደ ግል የሚተላለፉት የስራ እንቅስቃሴአቸው ሳይቋረጥ በመሆኑ ትመና ተሰርቶ ጨረታ በወጣው የንብረት ዝርዝርና ርክክብ በሚደረግበት ወቅት ልዩነት ስለሚኖር የጨመረ ንብረት ሲገኝ ተተምኖ እንዲከፈልበት እንደሚደረግ ፣ በኦዲቱም የቀረቡት ክስተቶች ኤጀንሲው ወደ ግል ካዛወራቸው ከ300 በላይ ድርጅቶች ውስጥ ከ2 እና 3 የማይበልጡ ስህተቶች መሆናቸውን ፣ ኮከብ ዱቄትን በተመለከተ የድርጅቱ ንብረት ያልሆኑ የሌላ ድርጅት ንብረት በሶፍት ኮፒ ልውውጥ ወቅት በስህተት ጨረታ ሰነድ ውስጥ ተካተው መገኘታቸውና ለባለሀብቱም ተገቢ ምላሽ እንደተሠጠው ፣ አዲስ አበባ ራስ ሆቴልን በሚመለከትም በማነስ የተገኘው ተሽከርካሪ በራስ ሆቴል ድርጅት ስር ሲተዳደር የነበረው የከረዩ ሎጅ የተረከበው የፌዴራል መ/ቤት አስቀድሞ ተረክቦ የወሰደ በመሆኑ ፣ ልዩነት መፈጠሩን ፣ የሕንጻ እድሳት ወጪውም የሆቴሉ ትመና ከተሰራ በኂላ ውል በመግባት የወጣ የእድሳት ወጪና በቋሚ ንብረት ላይ ዋጋ የሚጨምር በመሆኑ እንዲከፈልበት የተጠየቀ ትክክለኛ ጥያቄ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት ልዩነቶችን ለመቀነስ ተገቢው ጥንቃቄ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

41. ሆኖም በኦዲቱ የታየው የሁለት ድርጅቶች የርክክብ ልዩነት የተገኘው በናሙና ተመርጠው ከታዩ 18 የልማት ድርጅቶች ውስጥ እንጂ በጠቅላላ ከተሸጡት መካከል ባለመሆኑ ቁጥሩ ጉልህ አይደለም ለማለት አያስችልም፡፡ በተጨማሪም ከመረጃዎቹ ለመረዳት የሚቻለው ኤጀንሲው ለባለሀብቶች በሚያቀርባቸው የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ የንብረት ዝርዝሮች ትክክለኛነት በሚገባ የማይታይባቸውና ክለሳ የማይደረግበት ሁኔታ መኖራቸውን ፣ ልዩነቶችም ሲከሰቱ ማስተካከያው ሁለቱንም ወገን የማያካትት መሆኑን ነው፡፡

42. ይህም ባለሀብቱ በገዛው ድርጅት የስራ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከማሳደሩም በላይ ኤጀንሲው በቀጣይ ለሚሸጣቸው ድርጅቶች በተጫራቾች ዘንድ አመኔታን የሚያሳጣ በመሆኑ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች

የተጠናቀረ ዝርዝር መረጃ በኤጀንሲው ስለመኖሩ፤

43. በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች መረጃ በአግባቡ ተሰብስቦ በኤጀንሲው በመረጃነት የሚጠበቅበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል::

44. በኦዲቱ ወቅት የተገኘው የሰነድ ማስረጃ ከ1987-1997 ባሉት አስር አመታት 213 ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ወደ ግል ሲዛወሩ 3.13 ቢሊዮን ብር እና ከ1998-2003 ደግሞ 97 ድርጅቶች እና ቅርንጫፎች ወደ ግል ሲዛወሩ 5.6 ቢሊዮን ብር በድምሩ ባለፉት አስራ ስድስት ዓመታት 310 የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በጨረታ ሽያጭና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ግል ተዛውረው ብር 8.7 ቢሊዮን ገቢ እንደተገኘ ያሳያል፡፡

45. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት ጥቅል ማስረጃ ቢኖርም ፣ በአጠቃላይ የተሸጡትን 310 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሟላ ዝርዝር ማስረጃ በኤጀንሲው ማግኘት አልተቻለም፡፡

46. የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ለጉዳዩ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው በመስከረም 2004 ዓ.ም ባዘጋጀው ብሮሸር ላይ የተቀመጠ ጥቅል ወደ ግል የተዛወሩ የልማት ድርጅቶች ብዛትና ለኦዲቱ ስራ ተጠይቆ በተሰጠ የድርጅቶቹ ዝርዝር መካከል የተፈጠረ የቁጥር ልዩነት መንስኤ አንድ ገዢ የገዛቸው እና በተለያየ ቦታ የሚገኙ ቅርንጫፎች አንድ ላይ የተመዘገቡ መሆናቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በኤጀንሲው ከሚታተም መጽሄት (ዜና ፕመልድተኤ 2005) የተገኘ የድርጅቶች ዝርዝር መረጃ ቀርቧል፡፡

47 በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ ላይ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ በኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ በተራዘመ ክፍያ የተሸጡና የሚጠበቅባቸውን ክፍያ የጨረሱ ድርጅቶች ዝርዝር ለኦዲት ስራው አለመቅረባቸውን እንደማያውቁ ገልጸው ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ባዘዙት መሰረት በደብዳቤ ቁጥር 30/ሐ8/4/59/2006 በቀን ጥር 20/2006 በዲፈርድ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች ውስጥ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ የ48 የልማት ድርጅቶች ዝርዝር የቀረበ ሲሆን የኦዲቱ ጊዜ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቀረበው ማስረጃ ላይ ዝርዝር ትንተና ለመስራት አልተቻለም፡፡

48. በመሆኑም በኦዲቱ መግቢያ ጀምሮ እየተጠየቀ የነበረ ማስረጃ በወቅቱ አለመቅረቡ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ኃሳቦች

በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በኤጀንሲው የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን ፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ ቀልጣፋ እና ውጤታማነት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

49. በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ የተዘጋጀና ተግባራዊ የተደረገ የአሰራር መመሪያ በኤጀንሲው ስለመኖሩና አሰላሉ በሶፍትዌር የታገዘ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ተደርጎ፤

    በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ ኤጀንሲው ለሂሳብ አሰላል የሚጠቀመው የሽያጭ ውልና በተለያየ ጊዜ የጸደቀ የአሰራር መመሪያ ቢኖረውም አንድ ወጥ የሆነና ተቀናብሮ የጸደቀ አለመሆኑ እንዲሁም አሰላሉን የሚያግዝ ዘመናዊ ሶፍትዌር አለመኖሩ፣

50. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ለሚሸጣቸው ድርጅቶች የሚያዘጋጀው ውል አስፈላጊ የውል ግዴታዎችን መያዝና በውሉ መሰረት ባይፈጸም ጉዳዩን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ በግልጽ አለመቀመጡን በተመለከተ፣ የሚፈለግባቸውን አመታዊ ክፍያ በገቡት ውል መሰረት ባይፈጽሙ ጉዳያቸው ወደ ህግ የሚሄድበት የጊዜ ገደብ በተመለከተ መመሪያ አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን ሊከታተል እንደሚገባ፣

51. በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግን ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል በኤጀንሲው የተዘረጋ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት ስለመኖሩ በኦዲቱ ሲጣራ፤

    - ኤጀንሲው ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የሚፈለግባቸውን ቀሪ ሂሳብ በወቅቱ እንዲከፍሉ አመታዊ የክፍያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት በደብዳቤ ፣ በቦታው ድረስ ሄዶ በመነጋገርና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብ መሆኑን፣

- ቀሪ እዳን ከመክፈል አንጻር በታዩ ችግሮች ዙሪያ ለባለሀብቶች መጠይቅ በመበተን ኤጀንሲው ጥናት ማድረጉን፣
- ይህም ሆኖ ግን እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም. ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ከሃያ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ቀሪ ሂሳብ ብር 362,394,242.11 (ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) እና ፓውንድ 300,318.06 (ሶስት መቶ ሺህ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ከዜሮ ስድስት ፓውንድ) ከሁለት ወር እስከ አምስት አመት የዘገየ ሂሳብ መኖሩን፣

52. የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው በኦዲቱ ሲጣራ፤

- በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ ነገር ግን በርክክብ ወቅት በተደረገው ቆጠራ ያልተገኙ ንብረቶች መኖራቸው፣
- ይህም ሆኖ ባለሀብቶቹ ለተገኘው የንብረት ርክክብ ጉድለት ማካካሻ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም ፣ በጉድለት ለተገኙ ንብረቶች ተመላሽ እንዲሆን ወይም ማስተካከያ እንዲሰራ በውል ስምምነቱ ስላልተካተተ ማስተካከያውን ለመስራት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩ በኤጀንሲው መገለጹ፣

53. በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተጠናቀረ ዝርዝር መረጃ በኤጀንሲው ስለመኖሩ ሲጣራ ፣ ከ1987-2003 ባሉት አስራ ስድስት ዓመታት 310 የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በጨረታ ሽያጭና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ግል ተዛውረው ብር 8.7 ቢሊዮን ገቢ እንደተገኘ ጥቅል መረጃ ቢኖርም በኦዲቱ ወቅት የእነዚህን ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ኮፒ እና በሰነድ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ የታየ ሲሆን በአጠቃላይ በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶች ሊያርሙና በኤጀንሲው የተሻለ አሰራር እንዲኖር ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ኃሳቦች

ከላይ ለተመለከቱት የኦዲት ግኝቶችና የመደምደሚያ ኃሳቦች የሚከተሉት የማሻሻያ ኃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ❖ በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ በኤጀንሲው ስለመኖሩና አሰላሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆኑን በተመለከተ ኤጀንሲው ለአሰላል የሚጠቀምባቸውን መመሪያዎች በማቀናጀት አንድ የአሰራር መመሪያ ሊቀርጽና አጽድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በሂደት ላይ ያለውን የሶፍትዌር ቀረጻ ሊያፋጥን ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ የገዙ ባለሀብቶች ክፍያቸውን በወቅቱ ባይፈጽሙ ወጥ በሆነ አሰራር እንዲጠየቁ ለማድረግ እንዲቻል ኤጀንሲው የጊዜ ገደቡን በተመለከተ መመሪያ አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ❖ በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግን ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል በኤጀንሲው የተዘረጋ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ ኤጀንሲው የዓመታዊ የክፍያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት እንዲፈጽሙ ለማስታወስ በደብዳቤ ፣ ቦታው ድረስ ሄዶ በመጎብኘትና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ፣ እንዲሁም ቀሪ እዳን ከመክፈል አንጻር በታዩ ችግሮች ዙሪያ ለባለሀብቶች መጠይቅ በመበተን ኤጀንሲው ጥናት ማድረጉን ህዳር 2005 ዓ.ም ከቀረበ ሪፖርት መረጃ ቢገኝም ፣ ከድርጅቶቹ የሚፈለገው ቀሪ እዳ ከፍተኛ በመሆኑ ኤጀንሲው የፍርድ ሂደቱ የሚፋጠንበትን ሁኔታ ጭምር በመፈለግ የጀመረውን ጥረት ሊቀጥል ይገባል፡፡
- ❖ ባለሀብቶች በጨረታ የሚሸጡ የልማት ድርጅቶችን ተጫርተው ለመግዛት ከጨረታ ሰነዱ ጋር የሚያቀርቧቸው ቢዝነስ ፕላኖች የሚገቡትን ግዴታ ለመፈጸም የሚያስችላቸው ስለመሆኑ በኤጀንሲው የሚደረግ ግምገማ መኖሩን በተመለከተ፤ በባለሀብቱ የሚቀርቡ

ቢዝነስ ፕላኖች ተአማኒነት ያላቸውና የሌላቸው ከግንዛቤ እንዲገቡ በባለሙያ እገዛ ቢገመገም በድርጅቶች የተሻለ አፈጻጸም እንዲመዘገብና ከየድርጅቶቹ የሚፈለግ ሂሳብ ወቅቱን እየጠበቀ እንዲሰበሰብ ሊያግዝ ይችላል፡፡

- ❖ የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በተመለከተ ፣ የሚሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሚሰፍሩ መረጃዎች በቆጠራ ወቅት ከሚገኙት ንብረቶች ጋር የሚያሳዩት ልዩነት የሰፋ እንዳይሆን ድርጅቶቹ ለጨረታ ከመቅረባቸው በፊት የመረጃው ትክክለኛነት ሊጣራና የርክክብ ሂደቱም ሊፋጠን ይገባል፡፡
- ❖ በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተጠናቀረ ዝርዝር መረጃ በኤጀንሲው መኖሩን በተመለከተ በኤጀንሲው የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ዝርዝርና የተሸጡበት ዋጋ ፣ በተለይም በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ ወቅታዊ /Update/ እየተደረገ በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርቡ መረጃቸው በኤሌክትሮኒክስ ኮፒ እና በሰነድ ማስረጃ በኤጀንሲው ሊኖር ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲና መረጃ የተሰበሰበባቸው በናሙና የተመረጡ ድርጅቶች ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶች

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
1. ኤጀንሲው በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤	
1.1. ኤጀንሲው የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ አዋጅና ደንቡን መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣቱንና በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እንዲሁም በኤጀንሲውና በባለሀብቱ መካከል ግንኙነት የሚፈጥሩ ሰነዶች ትክክለኛና ወቅታዊ መሆናቸውን መገምገም::	1.1.1 ኤጀንሲው ባለሀብቶች የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ በሚገዙበት ወቅት ባቀረቡት የቢዝነስ ፕላን መሰረት ለመስራትና ውጤታማ ለመሆን እንዳይችሉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በጥናት በመለየት ሊሻሻሉ የሚገባቸውን የህግ ማዕቀፎች ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ለተግባራዊነቱ ሊሰራ ይገባል:: 1.1.2 ኤጀንሲው የተሸጡ የልማት

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
	ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብ ሂደት ቀልጣፋና ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል፣ ተጠያቂነትን የሚያጠናክርና የሚተገበር የአሰራር መመሪያ ሊኖረውና ተግባራዊነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡
	1.1.3 ኤጀንሲው ወደግል ይዞታ የሚዘዋወሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ዝርዝር ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቅርቦ ሊያስወስወንና የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን ሁሉ ሊያከናውን ይገባል፡፡
	1.1.4 ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ የልማት ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የገቧቸውን ግዴታዎች ማክበራቸውን ሊያረጋግጥና ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡
	1.1.5. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ወደ ግል ከተዛወሩ ድርጅቶች ስለሚሰበስበው ቀሪ የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ በተመለከተ ስትራቴጂክ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	1.1.6. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
	እቅድ ሊያቅድና ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	1.1.7 ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ለጨረታ ሲያቀርብ ባለሀብቱ የሚያቀርበው ቢዝነስ ፕላን የሚገባውን ግዴታ ለመፈጸም የሚያስችለው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	1.1.8. ባለሀብቶች ሊከፍሉ የገቡትን ግዴታ መክፈል ያልቻሉበት ምክንያት ሊታወቅና አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
	1.1.9. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ወደ ግል ባለሀብቶች የተላለፉ ድርጅቶች ያለባቸውን ቀሪ የሽያጭ ሂሳብ የሚከፍሉበትን የጊዜ ሰሌዳ (መርሃ ግብር) ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ ይገባል፡
	1.1.10. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በሚያቀርባቸው የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎችን ወቅታዊነትና ትክክለኛነት ሰነዱ ለባለሀብቱ ከመቅረቡ በፊት ማረጋገጥ አለበት፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
	1.1.11. በተራዘመ ክፍያ ወደ ግል ባለሀብቶች የሚተላለፉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቅድመ ክፍያ ከተፈጸመና ውል ከተገባ በኂላ ርክክብ የሚፈጸምበትን የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጥና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	1.1.12. ኤጀንሲው በጨረታ ለሚሸጡ የልማት ድርጅቶች ባዘጋጀው የውል ስምምነት ላይ የሚታየውን የአፈጻጸም ክፍተት እየለየ የሚከልስበት ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡
	1.1.13. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ለሚሸጣቸው ድርጅቶች የሚያዘጋጀው ውል አስፈላጊ የውል ግዴታዎችን መያዝና በውሉ መሰረት ባይፈጸም ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
	1.1.14. ባለሀብቶች ለጨረታ የቀረቡ ድርጅቶችን ከመጫረታቸው በፊት የቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚያገናዝቡበት በቂ የጉብኝት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
	1.1.15. በክትትልና በቁጥጥር በተለይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በቀረቡት የኦዲት ግኝቶች ላይ በወቅቱ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
	1.1.16. በወቅቱ ክፍያ ባለመፈጸማቸው ምክንያት ክስ የተመሰረተባቸው ድርጅቶች የህግ አፈጻጸም ሂደት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡
	1.1.17. በሽያጭ ዋጋ ውስጥ ታሳቢ ያልተደረጉና በርክክብ ጊዜ የታዩ ንብረቶች ዋጋ በትክክል መያዝ ይገባቸዋል፡፡
	1.1.18. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች ወደግል ሲዛወሩ አፈጻጸማቸውን ለመከታተልና ለመደገፍ የሚያስችለው ተገቢ አቅም ሊኖረው ይገባል፡፡
1.2ኤጀንሲው በሽያጭ ወደ ግል የተላለፉ የልማት ድርጅቶች ሂሳብን ባለሀብቶቹ በገቡት የሽያጭ ውል መሰረት ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል ፣ ለመቆጣጠርና ያለባቸውን ቀሪ ክፍያ አጠቃለው	1.2.1. በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት እንዲሰበሰብ ኤጀንሲው በቂ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
ማስገባታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡	
	1.2.2. በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች መረጃ በአግባቡ ተሰብስቦ በኤጀንሲው በመረጃነት የሚጠበቅበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል::
	1.2.3. በድህረ-ፕራይቬታይዜሽንና በፋይናንስና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት የሚገኙ ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ የሚያዙ የጋራ የሆኑ መረጃዎች እርስ በእርስ የማይቃረኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡
	1.2.4. በተራዘመ ክፍያ ወደ ግል አልሚ የተዛወሩ የልማት ድርጅቶች ቀሪ ክፍያ የሂሳብ አሰላል ላይ የሚያጋጥም ችግርን ለመፍታት አሰላሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
	የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡
	1.2.5. የልማት ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ የገዙ አልሚዎች የሚጠበቅባቸውን ክፍያ ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከመውሰዳቸው በፊት የሚፈለግባቸውን ቀሪ ክፍያና ማንኛውንም እዳ ያጠናቀቁ መሆናቸው በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	1.2.6. ኤጀንሲው በተሸጡ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ አሰባሰብ ላይ ያለውን የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ እንዲችል ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኙና የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡
2. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በተራዘመ ክፍያ ከገዙ ባለ ሃብቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥና መደበኛ የመወያያ መድረክ እንዲኖር የዘረጋውን የአሰራር	2. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ አሰባሰብ ለማፋጠን እንዲረዳው ባለ ሀብቶችና ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ለመስራትና የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅና ከመድረኩ የተገኙ ማስተካከያ የሚፈልጉ ጉዳዮችን

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች	የኦዲቱ መስፈርቶች
ስርዓትና ተግባራዊነቱን መገምገም፡፡	እየለየ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

አባሪ 2

እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም.ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ሂሳብ ያለባቸው

የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር መግለጫ

ተ.ቁ.	የተሸጡ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር	የተሸጡበት ጊዜ	ክፍያው የተራዘመበት የጊዜ ገደብ	ክፍያው መጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ	ክፍያው የዘገየበት ጊዜ	እስከ ህዳር 30,2006 ዓ.ም መጠናቀቅየነበረበት ሂሳብ	አስተያየት
1.	ቦሌ ቡልቡላ ጠጠር ማምረቻ ድርጅት	08/11/99	5 ዓመት	08/11/04	1 ዓመት ከ4 ወር	9,069,235.76	
2.	አዲስ ጡብ ማምረቻ አ/ማ	29/02/99	5 ዓመት	29/02/04	2 ዓመት ከ1ወር	5,080,401.44	
3.	አዲስ አበባ ቆዳ	8/3/1999	5 ዓመት	08/03/04	2 ዓመት	24,959.82	
4.	አዳኣ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ	06/07/99	2.6 ዓመት	06/01/02	3 ዓመት ከ2ወር	2,977.60	
5.	የረር ዱቄት ፋብሪካ	01/04/00	1 ዓመት	01/04/01	5 ዓመት	3,123,447.33	
6.	የአሳ ምርትና ገበያ ድርጅት	19/02/00	5 ዓመት	19/02/05	1 ዓመት ከ1ወር	15,657,543.75	
7.	ሐዋሳ ዱቄት					15,695,933.72	በድጋሜ ጨረታ

	ፋብሪካ						ወጥቶ ለሌላ ባለሀብት የተሸጠ
8.	የውሀ ስራዎች ድርጅት	16/06/02	5 ዓመት	16/06/07	6 ወር	436474.31	
9.	ኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካ	15/03/02	3 ዓመት	15/03/05	1 ዓመት	300,318.06 Pound	
10.	ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ	13/08/02	5 ዓመት	13/08/2007	1 ዓመት ከ8 ወር	36,330,210.77	
11.	ኢትዮ ጃፓን የናይለን ጨርቃጨርቅ አ/ማ	19/09/02	5 ዓመት	19/09/07	3 ዓመት ከ6 ወር	18,689,963.73	
12.	ሐረር ራስ ሆቴል	22/11/03	4 ዓመት	22/11/07	1 ዓመት	1,504,530.36	
13.	ኢትዮጵያ ብረታብረት ማቅለጫ	28/12/02	5 ዓመት	28/12/07	1ዓመት ከ9 ወር	38,466,586.33	
14.	ኢትዮጵያ ሆቴል	10/05/03	5 ዓመት	10/05/08	11 ወር	1,602,347.13	
15.	አዳማራስ ሆቴል	18/05/03	5	18/05/08	10 ወር	637,487.31	

			ዓመት				
16.	ትግራይ ዱቄት ፋብሪካ	01/10/03	5 ዓመት	01/10/08	1 ወር	100,404.13	
17.	ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ	02/10/03	5 ዓመት	02/10/08	2 ዓመት ከ5ወር	16,919,723.85	
18.	ሐዋሳ ዱቄት ፋብሪካ	05/11/03	5 ዓመት	05.11.2008	2 ዓመት ከ6ወር	15,943,764.61	
19.	ምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ	07/01/02	5 ዓመት	07/01/07	1 ወር	29,201.89	
20.	ታቦር የሴራሚክ ውጤቶች አ/ማ	29/11/03	5 ዓመት	29/11/08	5 ወር	15,629,400.71	
21.	የቤቶች ማምረቻ ድርጅት	19/11/03	5 ዓመት	19/11/08	2 ወር	437,385.14	
22.	ብሄራዊ ሲሚንቶ	15/11/02	5 ዓመት	15/11/07	8 ወር	19,158,979.92	
23.	ሰንቀሌ ኖራ				1ዓመት ከ9 ወር	363,529.54	

24.	ቃሊቲ ብረታብረት	11/10/04	5 ዓመት	11/10/09	3 ወር	4,922,193.19	
25.	አዲስ አበባ ራስ ሆቴል	**22/02/04**	4 ዓመት	21/02/04	2 ዓመት	43,897,069.42	
26.	ደብረብርሀን ብርድልብስ ፋብሪካ	10/05/01	ዓመት	10/05/01	2 ዓመት ከ3ወር	2,087,700.86	
27.	ደሴ አምባሰል ግዮን ሆቴል	22/05/04	5 ዓመት	09/05/09	1ዓመት ከ1 ወር	790,093.43	
28.	መካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት	28/11/03	5 ዓመት	27/11/08	2 ዓመት	95596087.04	
2.	ኤረር ጎታ እርሻ ልማት	13/12/02	5 ዓመት	12/12/07	4 ወር	196,609.02	
						362,394,242.11 እና 300,318.06 Pound	